


# ዘላቂ የአውሮፕላን ማረፊያ መሠረተ ንድፍ/ፕላን ሁኔታ

የሲያትል-ታኮማ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ (SEA) ዘላቂ የአየር ማረፊያ ዋናው ንድፍ/ፕላን (SAMP) በ2018 ተጠናቀቀ። ከSAMP፣ ወደቡ 31 በቅርብ ጊዜ የሚከናወኑ መርሐግብሮችን Near-Term Projects (NTPs) አይታ እና የአካባቢ ግምገማ (2018) የማጠቃለያ ሂደቱን አጠናቅቋል።

በአሁኑ ወቅት የብሔራዊ የአካባቢ ጥበቃ ቋሚ መመሪያ/ፖሊሲ (NEPA) የአካባቢ ጥበቃ ግምገማ በመካሄድ ላይ ነው, የ NEPA ረቂቅ ሰነድ በበልግ 2024 ይወጣል ተብሎ ይጠበቃል. የ NEPA ሂደቱ እንደተጠናቀቀ፤ የግዛቱ የአካባቢ ጥበቃ ቋሚ መመሪያ /ፖሊሲ (SEPA) ግምገማ ይከተላል።

## የአውሮፕላን ማረፊያ መሠረተ ንድፍ/ፕላን ምንድን ነው?

የኣውሮፕላን ረፍይ ማመሠረተ ንድፍ/ፕላን አጠቃላይ የኣውሮፕላን ማረፍይውን ለወደፊት እድገት እና መሻሻል የሚገልጽ የረጅም ጊዜ እቅድ ሰነድ ነው። ኣይሮፕላን ማረፍያው እንዲያድግ እና በብቃት በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ከወደፊቱ ፍላጎቶች ጋር እንዲላመድ በማድረግ እንደ ስልታዊ ንድፍ/ፕላን ሆኖ ያገለግላል። እነዚህ በአብዛኛው በየ 10 ዓመቱ ይከሰታሉ።

## የአውሮፕላን ማረፊያ መሠረተ ንድፍ/ፕላን ዋና ዋና ክፍሎች-

ነባር ሁኔታዎችን ለይቶ ማወቅ፡ በአሁኑ ጊዜ ያሉትን የመተላለፊያ መንገዶች፣ ታክሲዎች፣ የመተላለፊያ ጣቢያዎችና ሌሎች ተቋማት ይገልጻል።

የወደፊቱን እንቅስቃሴ ምን ሊሆን እንደሚችል ግምት ውስጥ በማስገባት:- የተሳፋሪዎች፣ በረራዎች፤ ጭነትን እና ማናቸውንም ገደቦች አሁን ባለው ወይም በታቀደው የኣውሮፕላን ማረፊያው መገልገያዎች መሠረተ ልማት ላይ በመመርኮዝ ይገነባል።

የመገልገያ መስፈርቶች :- አዲስ ወይም የተሻሻሉ መገልገያዎች፤ እንደ የአውሮፕላን መንደርደሪያ፣ ተርሚናሎች፣ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች እና ለጥገና የሚይስፈልጉ ቦታዎች አስፈላጊነት መለየት።

ዘላቂ የአውሮፕላን ማረፊያ መሠረተ ንድፎች/ፕላኖች፤ እነዚህን የአውሮፕላን ማረፊያ ዋና እቅድ ንጥረ ነገሮች በምንገነባበት፣ በምንገነባበት መንገድ፣ እና ንድፎችንፕሮጀክቶችን በምንሠራበት መንገድ ላይ ትኩረት በማድረግ ያካትቱታል።

አማራጮችን መለየት:- ምርጥ መፍትሄዎችን ለማግኘት የአውሮፕላን ማረፊያ ልማት የተለያዩ አማራጮችን ይገመግማል።

የመተግበር እና የገንዘብ ነክ አፈፃፀም:- የተለያዩ እቅዶች/ፕሮጀክቶች እና ማሻሻያዎች የሚጠናቀቁበትን ጊዜ እና የነዚህን እቅዶች/ፕሮጀክቶች ወጪ እና ሊሆኑ የሚችሉ የገንዘብ ምንጮችን የጊዜ ሰሌዳ ያቀርባል።

. አሁን ያሉ አካባቢያዊ ሁኔታዎች:- እቅዶች/ፕሮጀክቶች በሚቀርቡበት እና በአካባቢው ያለው ወቅታዊ የአካባቢ ሁኔታዎችንም ይለያል።

## የአውሮፕላን ማረፊያ መሠረተ ንድፍ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?


- የአውሮፕላን ማረፊያዎች እድገት ለማድረግና በአየር ጉዞ ፍላጎት ላይ ለውጥ ለማድረግ እቅድ እንዲፈጥሩ ይረዳል።
- አስተማማኝና ውጤታማ በሆነ መንገድ መሥራት እንደሚችሉ ያረጋግጣል።
- የአውሮፕላን ማረፊያ መስፋፋትን ወይም ለውጦችን በተመለከተ አስተያየቶችን በመሰብሰብና አስተያየት በመስጠት ማህበረሰቡን ያጠቃልላል።
- ለአውሮፕላን ማረፊያ ማሻሻያዎች የገንዘብ ድጋፍ እና የተሳትፎ ድጋፍ ለማግኘት ይረዳል።

ንድፍ NEPA EA በኦክቶቨር 21፣ 2024 ይታተማል፣ የሕዝብ አስተያየት ጊዜ ዲሴምበር 513፣ 2024 ያበቃል። በSAMP ላይ ወቅታዊ መረጃ ያግኙ እና እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ ይወቁ፡

**sampntpenvironmentalreview.org**

# የአካባቢ ግምገማ

## የአካባቢ ግምገማ ሂደትን መረዳት




የአካባቢ ጥናት በፖርት ኦፍ ሲያትል ህንፃዎች እቅዶች/ፕሮጀክቶች የአየር ጥራት እና የአየር ንብረት፤ የውሃ ሃብት፤ ስነዮታዊ ቁጥጥር፤ ሃብት እና ጫጫታን ጨምሮ በተለያዩ ምድቦች አካባቢን እንዴት ሊነካ እንደሚችል ለመገምገም ሂደት ነው። ተፅዕኖዎች ተለይተው ከታወቁ፤ትንታኔው የእነዚህን ተፅዕኖዎች መጠን ይገመግማል፤ እና አስፈላጊ ከሆነ፤ እነዚህን ተፅእኖዎች ለመቀነስ ወይም ለማስወገድ መንገዶች ይለይል። አንድ ንድፍ/ፕሮጀክት ሁለቱንም የፌዴራል እና የክልል የአካባቢ ግምገማዎችን ሊፈልግ ይችላል፣ ነገር ግን ሁለቱም ሁልጊዜ ለእያንዳንዱ ንድፍ/ፕሮጀክት አያስፈልጉም።

የአካባቢ ግምገማ ዓላማ የታቀደው ንድፍ/ፕሮጀክት ከመካሄዱ በፊት ሊያመጣ የሚችለውን የአካባቢ ተጽዕኖ ለመገምገም ነው። ቁልፍ ዓላማዎችም የሚከተሉትን ያካትታሉ፤


- በመረጃ ላይ የተመሰረተ- ውሳኔ
- በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ ሙሉ ግልፅነት እና የህዝብ ተሳትፎ
- ሕጎችንና ደንቦችን ማክበር
- ተጽዕኖዎችን ማስወገድ፣ መቀነስ ወይም ማቃለል የሚቻልባቸው መንገዶች መፈለግ

## በ NEPA የአካባቢ ግምገማ ሂደት ውስጥ ያሉ እርምጃዎች

የተለመደው የአካባቢይዊ ግምገማ ሂደት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

1. የእቅድ/ፕሮጀክቱን ዓላማ እና ፍላጎት ማዳበር እና መፍትሄዎችን ሊሰጡ የሚችሉ አማራጮችን መወሰን።
2. በብሔራዊ የአካባቢ ጥበቃ ደንብ ህግ (NEPA) ሰነዶች ውስጥ የተመለከቱትን ድርጅቶችን እና የህዝብ ጥያቄዎችን ለመረዳት ክልል በማድረግ።
3. በ NEPA ሰነድ ውስጥ ለተዘረዘሩት አማራጮች ሁሉ የአካባቢ ውጤቶችን መተንተን እና መመዝገብ።
4. 4. ረቂቅ EA ሰነድ ሲወጣ ህዝባዊ ስብሰባ ወይም ችሎትን ጨምሮ ከድርጅቶች፣ ከማህበረሰቡ እና ከመላው ህዝብ ግብአት ለመሰብሰብ ለመምከር እና ለመቀጠል ህዝባዊ ስብሰባዎችን በመተንተን ሂደት ማካሄድ።
5. የመጨረሻውን NEPA ሰነድ ለማዘጋጀት የሚረዳውን ረቂቅ NEPA ሰነድ ላይ አስተያየት መስጠት።
6. ከሁለቱም ግንባር ቀደም የፌደራል ድርጅት ጋር ያበቃል - በዚህ ጉዳይ ላይ FAA - ምንም ወሳኝ ተጽዕኖ/የውሳኔ መዝገብ ወይም የመሪ ድርጅት EIS እንደሚያስፈልግ የሚወስን ውሳኔ ይሰጣል።

በአካባቢያዊ የምርመራ ሂደት ወቅት የህዝብ አስተያየት በመደበኛ አስተያየት የሚሰጥበት ወቅት ነው። በዚህ ሂደት ወቅት የሕዝብ አስተዋጽኦ ዓላማ ከቀረቡት ፕሮጀክቶች ጋር የተያያዙ ተጽዕኖዎችን ሙሉ በሙሉ በመረዳት እና አንድ የፌዴራል ወኪል የመጨረሻ ውሳኔ ከማሳለፉ በፊት የህብረተሰቡን ስጋቶች ግምት ውስጥ ማስገባት መመርመር ነው። የ NEPA ሂደቱ እንደተጠናቀቀ፣ የግዛቱ የአካባቢ ጥበቃ ደንብ/ፖሊሲ (SEPA) ግምገማ ይከተላል።




ኖቬምበር 11፣ 2024 ተዘምኗል